# ጥንቸልና ዔሊ



10-13ኛው ሳምንት

2ኛ ክፍል

መጽሐፍ 7

# ጥንቸልና ዔሊ

መጽሐፍ 7 | 2ኛ ክፍል | 10-13ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ከዕለታት አንድ ቀን ጥንቸልና ዔሊ በሰፊ መስክ ላይ ጉዞ ጀመሩ:: በመስኩ ላይ ከሳር በስተቀር ቁጥቋጦ የለም:: አልፎ አልፎ ግን ትንንሽ ድንጋዮች ይታያሉ::



ጥንቸልና ዔሊ በጉዞ ላይ
እያሉ በወሬ ተመስጠዋል::
ጥንቸል በአጋጣሚ ወደኋላ
ዘወር አለች::



ጥንቸል አንድ አስፈሪ ነብር ወደነሱ ሲገሰግስ ተመለከተች::



እንዳየችው በጣም ደነገጠች::
ትንፋሽ አጠራት:: “ዔሊ!
ዔሊ! አንድ አስፈሪ ነብር
ወደ እኛ እየመጣ ነው”
አለቻት:: ዔሊም “እና ምን
ይሻላል?” ከማለቷ ጥንቸል
እግሬ አውጪኝ ብላ
ተፈተለከች::



ዔሊም ትንሽ አሰብ
አደረገች:: በመስኩ ካሉት
ትንንሽ ድንጋዮች መካከል
ገባች:: አንገቷን፣ ራሷንና
እግሯን ቅርፊት በመሰለ
አካሏ ደበቀች:: ራሷን ትንሽ
ቀና አድርጋ የሚሆነውን
ትጠባበቅ ጀመር::



ነብር የጥንቸልን ሩጫ እንደዋዛ ተመለከተ:: ሳቅ አለና ፍጥነቱን እጥፍ አደረገ::



ነብርና ጥንቸል አባራሪና
ተባራሪ ሆኑ:: ጥንቸል
አሁንም ዘወር አለች::



ከፊቷ ያለ ያላየችው ትንሽ ድንጋይ አደናቀፋት:: ወዲያውኑ ተዝለፍልፋ ወደቀች:: ድንጋጤና ድካም ሰውነቷን አዝለፈለፋት:: የልቧ ምት ጨመረ::



ከወደቀችበት መነሳት
አልቻለችም። ነብር ደረሰባት።
ዘሎ ጥፍሮቹን በጉሮሮዋ ላይ
አሳረፈባት።

USAID

ከአሜሪካን ህዝብ